

## ሔዋን፣ የመጀሪያዋ ሴት

- በስድስት ቀናት ውስጥ እግዚብሔር አለምንና በውስጧ ያሉትን ነገሮች ፈጥሮ አጠናቀቀ። የፈጠራቸው ፍጥረታትም ሆኑ ምድር ምንም እንከን አይወጣላቸውም ነበር። የተለያዩ አይነት ዛፎች፣ አበቦች፣ ሳርና እንስሳት ምድርን ሞልተዋት ነበር። የኤደን ገነትን ከሰራ በኋላም የሚንከባከባትንና የሚጠብቃትን ሰው ፈጠረ። ስሙም አዳም ይባላል። እግዚአብሔርም አዳምን እንዲህ አለው፣ "በኤደን ገነት ውስጥ ከሚገኙ የዛፍ አይነቶች በሙሉ ፍሬያቸውን መብላት ትችላለህ። ሆኖም *መልካምንና ክፉን ከምታስተውቀው* የዛፍ ፍሬ ግን አትበላም።" የዚያችን ዛፍ ፍሬ እንዲበላ አልተፈቀደለትም። ከበላ ግን እንደሚሞት ተነገረው።

- እግዚአብሔር ለተወሰኑ ጊዜያት ብቻውን እንዲኖር አደረገው። ስለዚህም ብቸኛ ነበር። ፍቅር የሚጋራውም ሆነ ከእርሱ ጋር የሚጨዋወት ሰው አልነበረም። በዚያን ጊዜ ብቸኛው ሰብአዊ ፍጡር እሱ ብቻ ነበር። እግዚአብሔርም ረዳት እንደሚያስፈልገውና ብቸኛ መሆን እንደሌለበት አየ። እግዚአብሔር ሔዋንን የፈጠረበት መንገድ ለየት ይላል። እንደምታስታውሱት እግዚአብሔር አዳምንና እንስሳትን የፈጠረው ከምድር አፈር ነበር። በዚህ ምትክ እግዚአብሔር ለአዳም ለየት ያለ እቅድ አውጥቶለት ነበር። ኃይለኛ እንቅልፍ እንዲወስደው ካደረገ በኋላ ከጎኑ አንድ አጥንት ወሰደና ሔዋንን ሰራት። አዳም ከእንቅልፉ ሲነቃ ሔዋንን አያት። እጅግ በጣም ተደነቀ። እንዲህም አለ፣ "ይህች አጥንት አጥንቴ፣ ይህች *ሥጋም ሥጋዬ* ናት።" በአንድ ላይ በጣም ደስተኞች ሆነው መኖር ጀመሩ።

- ሔዋን በኤደን ገነት መካከል ስላለችውና ፍሬዋ መበላት ስለሌለባት ዛፍ በሚገባ ታውቃለች። አዳም ወይንም እግዚአብሔር መብላት ስላለባቸውና ስለሌለባቸው ነገር እንደነገሯት ግልፅ ነው።

- አንድ ቀን ፈታኝ በእባብ መልክ ወደሔዋን መጣ። የጠየቃት ጥያቄም እንዲበሉ ስለተፈቀደላቸው ነገር ነበር። እሷም በገነት መካከል ካለችው አንድ የዛፍ ፍሬ መብላት እንደሌለባቸው ነገረችው። ከዚህች ፍሬ መብላትም ሆነ መንካት እንዳልተፈቀደላቸውና ቅጣቱም ሞት እንደሆነ ጨምራ ገለፀችለት።

- እባብም፣ “በእርግጥ አትሞቱም፣” አላት። አሁን እባብ ለሔዋን የነገራት ነገር እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ተቃራኒ ነገር ነበር። እግዚአብሔር ከዚህች ዛፍ ፍሬ በበሉ ቀን ልክ እንደእግዚአብሔር መልካሙንና ክፉውን ማወቅ ስለሚችሉ እግዚአብሔር እንዳይበሉ ከለከላቸው እንጂ በፍፁም እንደማይሞቱ ነግሮ አሳመናት። ከዚያን ሰዓት ጀምሮም ሔዋን ፍሬዋን በተለየ አይን ማየት ጀመረች። በጣም የሚያምርና ለመብላት የሚያስጎመጅ ፍሬ እንደሆነ አየች። እንዲሁም ከፍሬው ብትበላ እንደእግዚአብሔር እንደምትሆን ማሰቧንም ቀጠለች። በቀረበላት ፈተና ተረታች። ስለዚህም ከፍሬው ወሰደችና በላች። አዳምም ይህ ሁሉ ሲሆን አጠገቧ ነበር። ለእርሱም ደግሞ ከፍሬው ወሰደችና ለእርሱም ሰጠችው፤ እርሱም በላ። አዳም ስለሰራው ኃጢአት በሔዋን ላይ አሳበበ። ሔዋንም ደግሞ በበኩሏ ኃጢአቷን በእባብ ላይ አሳበበች።

- የበሉት አንድ ፍሬ ነበር። ቢሆንም የተከለከለ ፍሬ ነበር። እግዚአብሔር ፈተናቸው። ፈተናውን ግን ማለፍ አልቻሉም። ከአሁን በኋላ ነገሮች እንደቀድሞው አይሆኑም። በእነርሱ ኃጢአት ምክንያት ኃጢአት ወደአለም ገባ። የአዳም ስራም እንደዱሮው ቀላል አይሆንም። ምክንያቱም ምድር እሾኽና አሜኬላ ታበቅላለችና። ስለዚህም እርሻ ከመጀመሩ በፊት እሾኹንና አሜኬላውን ማስወገድ ይጠበቅበታል። ሔዋንም ልጅ ስትወልድ በአካሏ ላይ ሕመም ይሰማታል። እባብ ደግሞ በምድር ላይ እየተሳበ ይሄዳል።

- ከዚህ በኋላም ሕይወት እንከን የለሽ የሆነባትን የኤደን ገነትን ለቀው እንዲወጡ ተገደዱ። ሔዋን ልጅ መውለድ ጀመረች። በመጀመሪያ ቃየንና አቤልን ወለደች። ከዚያም ብዙ ወንዶችና ሴቶችን ወለደች። በምድር ላይ የኖሩና አሁንም በመኖር ላይ ሰዎች በሙሉ የተገኙት ከእነኝህ ሁለት ሰዎች ነበር። ሔዋን ምን ያህል እድሜ በምድር ላይ እንደኖረች አናውቅም። አዳም ግን በምድር ላይ 930 ዓመታት ከኖረ በኋላ ሞተ።

*ስለሔዋን በዘፍጥረት መፅሐፍ በምዕራፍ 2 እና 3 ላይ ማንበብ እንችላለን።*

http://gardenofpraise.com